# የዲያስፖራ ፖለቲካና ጽንፈኝነት...!

ክፍል ሶስትና የመጨረሻ
ገረመው

ትግራይ ኦንላይን April 19, 2014

የኢትዮጵያ አዛውንት የፖለቲካ ሰዎች የአንድ ዘመን ሰዎች ስለሆኑ ወይም ከግራ አስተሳሰብ ስለተቀዱ ላለመስማማት የተስማሙ አድርጎ የማየት አዝማሚያ ይስተዋላል፡፡ በእርግጥ ብዙ ኢትዮጵያውያን ከትምህርት ቤት ጀምሮ የመተዋወቅ ዕድል ገጥሟቸው ሊሆን ይችላል፡፡ የፅንፈኞች የፖለቲካ ቅኝት ግን ከዚሁ ታሪክ ጋር ግንኙነት የለውም፡፡

ፅንፈኞች ባለፉት 40 ዓመታት በተለያዩ የትግል ሜዳዎች ቆስለውና ተላልጠው ተሸንፈው ቂምና ቁርሾ ቋጥረው የተሰደዱ ወገኖች ናቸው፡፡ በደርግ የመጀመሪያዎቹ ዓመታት በአገር ቤት የነበሩ የፖለቲካ ቡድኖች ተራማጅ አስተሳሰብ የነበራቸው ቢሆንም ድርጅቶቹ ተሸንፈው ሲፈርሱ አባላቱ በወቅቱ ሲያራምዱት የነበረውን አስተሳሰብ ትተው ነገሮችን ከቂምና ከታሪክ አንፃር ብቻ ማየት ጀመሩ፡፡

በደርግ ዘመን ካድሬዎች ሆነው ሲሰሩ የነበሩ ወገኖች በእርግጥ ተሸንፈዋል፡፡ ሁሉም ባይሆኑም አንዳንድ የደርግ የጦር መኮንኖች ቂም ይዘው ተሰደዋል፡፡ የኢሠፓ ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት፣ የደርግ የኪነት ሰዎች፣ ጋዜጠኞች፣ በአጠቃላይ የሥርዓቱ የርዕዮተ ዓለም ጠበቆች የቂም በቀል ፖለቲካ አርግዘው ተሰደዋል፡፡

የፅንፈኞች ፖለቲካ በቂምና በጥላቻ የታጀበ በመሆኑ ለሠላማዊ ፖለቲካና ለሰጥቶ መቀበል የተዘጋጀ አይደለም፡፡ መንግሥት ለተቃዋሚ ሁሉ ግማሽ መንገድ ተጉዞ ለማስተናገድ ጥሪ ሲያቀርብ ፅንፈኞች ግማሽ መንገድ ርቀው ይሸሻሉ፡፡ የእነዚህ ወገኖች ፍላጎት አሁንም ማሸነፍ እንጂ በዴሞክራሲያዊ መርህ መሸናነፍን አይደለም፡፡ "ጅብ በማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" እንዲሉ ፅንፈኞች ዴሞክራት ነን እስከማለት የሄዱበት ሁኔታ እያየን ነው፡፡

ዛሬ ፅንፈኞች በሚቆጣጠሩት ሚዲያ በኩል ተሰምቶ የማያውቅ ዘረኝነትና ጥላቻ እየተሰበከ ነው፡፡ እነዚህ ወገኖች ይህን የሚያደርጉት "ለኢትዮጵያ አንድነት" ብለን ነው ይሉናል፡፡ የኢትዮጵያ አንድነት ከጥላቻ ፖለቲካ ነፃ የሆነ አስተምህሮን ይጠይቃል፡፡ ለኢትዮጵያ አንድነት የሚታገል ወገን የተወሰነ ሥነ ምግባር ዴዜደራታ ያስፈልገዋል፡፡ በአንድ ብሔር ላይ ጥላቻ የሚሰብክ ቡድን የአንድነት ኃይል ሊሆን አይችልም፡፡ አንድን ህይማኖት ከሌላው እንዲጋጭ የሰበከ ቡድን በምን ዓይነት ሁኔታ የአንድነት ሀይል ተብሎ ሊገመት ይችላል? የአንድነት ኃይል ማለት ከዴሞክራሲዊ አንድነት ውጭ ማሰብ ይቻል ይሆን? ይህ ሊሆን አይችልም፡

ፅንፈኛው ከሌሎች ወገኖች ጋር ለመግባባት ያልቻለበት ምክንያት ከልጅነት ጀምሮ ሌሎችን በመናቅ የተጠመቀና ከሌሎች ጋር በአንድ ማዕድ አልበላንም የሚለውን አባባል እየተማረ ያደገ በመሆኑ ብቻ አይደለም፡፡

ፅንፈኛ በተለያዩ ጊዜያት በአገር ቤት ፖለቲካ እጁን አስገብቶ የተሸነፈና የቆሰለ በመሆኑም ብቻ አይደለም፡፡ በደረሰበት ሽንፈትና ውርደት ቁርሾና ቂም በመቋጠሩም ብቻም አይደለም፡፡ በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት የተገኘችውን የአገሪቱን ጥሪት ለልማት ሲያውል በማየቱ ኪራይ ሰብሳቢ በመሆኑም ብቻ አይደለም፡፡ ፅንፈኞች ከእነሱ ውጭ ሌሎች ወገኖች ጥራት የላቸውም ከሚል አስተሳሰብ ብቻ አይደለም፡፡

ፅንፈኛው በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ግትር አቋም የሚያራምደው የትም ፍጪው ዱቄቱን ወይም ሥልጣኑን አምጪው ከሚል አስተሳሰብ ብቻ በመነሳትም አይደለም፡፡ በአገር ቤት ዴሞክራሲ እየተጠናከረ በሄደ ቁጥር የተስፋ መቁረጥ ጨለምተኝነት ስለተጫነው ብቻም አይደለም፡፡

ፅንፈኛው በሁሉም ዓይነት በሽታዎች የተተበተበ መድሀኒት የለሽ፣ ሠላም ዴሞክራሲና ልማት የሚባሉ ሥነ-ሐሳቦችን ለማድመጥ አቅም የጎደለው፣ ለሠላማዊ ፖለቲካ ያልተዘጋጀ፣ በነውጥ ወይም በትጥቅ ትግል ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን ለመናድ የተዘጋጀ በመሆኑም ጭምር ነው፡፡ የአገራችን ፖለቲካም በሁለት ጫፎች የተወጠረ (polarized) እንዲሆን በሁለቱም ጫፎች መካከል ያለውን ሰፊ ሥፍራ ለመርገጥ ፈቃደኝነት የጎደለው ወገን በመሆኑ ነው፡፡

በዲያስፖራው የፖለቲካ ሰዎች የተመራ የፖለቲካ ቡድን በአገር ቤት በተካሄዱት ለውጦች እዚህ ግባ የሚባል አዎንታዊ አስተዋፅኦ አልነበረውም፡፡ የዲያስፖራ ጫና ያለበት አገር በቀል የፖለቲካ ቡድንም ውሎ አድሮ በዲያስፖራው መነዳቱ ስለማይቀር አጥር ጥሶ መውጣቱ አልቀረም፡፡ የዲያስፖራው የፖለቲካ ስብስቦች ከሕዝብ የተነጠሉ ስለሆኑ የጥቂት ልሂቃን መደበሪያና ጊዜ ማሳለፊያ ከመሆን አያልፉም፡፡

የቡድኖቹ ዓላማም በሰበብ አስባቡ የዲያስፖራውን ጥሪት ለመመዝበር እንደሆነ ነው፡፡ የዲያስፖራ ወገኖች ከአገር ርቀው በመኖራቸው ብቻ ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ የፖለቲካ አስተሳሰብ እና ፕሮግራም ሊኖራቸው አይችልም፡፡ ይህም በመሆኑ በአገር ቤት ፖለቲካ ለመሳተፍ ሲሞክሩ ራሳቸው ተሳስተው ሌላውን ሲያሳስቱ ይስተዋላል፡፡

ዲያስፖራው በአገር ቤት ፖለቲካና ማሕበራዊ ህይወት ንቁ ተሳትፎ ያደርግ ዘንድ ሁኔታዎች መመቻቸት እንዳለባቸው ይህ ፅሁፍ ጠቁሟል፡፡ ዲያስፖራው ከአቅሙ በላይ የሆነውን ፖለቲካ ለመምራት ከመሞከር ይልቅ በኢኮኖሚውና በልማት ቢሳተፍ የተሻለ አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችል ማየት ይቻላል፡፡

በፖለቲካ ሂደት ያለው ተሳትፎ በአገራዊ አጀንዳዎች ለሠላምና ለዴሞክራሲ ለዘላቂ ልማት ድጋፉን ቢሰጥ የተሻለ መግባባት ሊፈጥር እንደሚችል አመላክቷል፡፡ ከዚህ ውጭ በፖለቲካው ዘርፍ ለመሳተፍ የሚፈልግ ወገን ግን ኑሮውን በውጭ እስከቀጠለ ድረስ የፖለቲካ አመራር ለመስጠት ባይቃጣው ይመከራል፡፡

“የአገሩን ሰርዶ በአገሩ በሬ” የሚለው አባባል የትም ቦታ ሊሰራ ይችላል፡፡ በመጨረሻም የዲያስፖራው ፅንፈኞች የራሳቸውን መንገድ ዘግተው የሌላውን መንገድ እንዲዘጉ መፈቀድ የለበትም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይማር ያስተማረን በመሆኑ ሁሉም ወገን ብድር ይመልስ ዘንድ ሀላፊነት አለበት፤ የሚለብሰው የሌለው ሰው ደግሞ ደጋግሞ ሲያለብሰን ትርጉሙን ማሰብ ይጠይቃል፡፡ የሞራል እና የሥነ ምግባር ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ዲያስፖራ ከአገሩ ጋር ያለውን ጤነኛ ግንኙነት ከፅንፈኞች ጠብቆ የራሱን ማሕበራዊ ካፒታል ለማስፋትና ለማጠናከር የተወሰኑ መሠረታዊ የህይወት መርሆዎች ያስፈልጉታል፡፡ ከሌሎች የዲያስፖራ ወገኖች ታሪክና ልምድ ለመማር ፈቃደኛ መሆን ይጠይቃል፡፡ ከአገር ቤት ጋር ያለውን ተፈጥሯዊና ማሕበራዊ ግንኙነትም ይጠናከር ዘንድ የኢትዮጵያዊነት እሴት እየተጠናከረ መሄድ መቻል አለበት፡፡

ይህ ይሳካ ዘንድ የተወሰኑ የጋራ የሥነ ምግባር እሴቶች መከተል የግድ ይለናል፡፡ ኢትዮጵያዊነት በየወቅቱ እየታደሰ የሚሄድ ነው፡፡ የሽረት-ሽረት ሕግን ተከትሎ እየተገነባ የሚሄድ ነው፡፡ አንድ ወቅት የነበረ ገዥ እሴት እየተሸረሸረ በአዲስ መተካቱ አይቀሬ ነው፡፡ አዲሲቷን እና የነገዋን ኢትዮጵያን ከዴሞክራሲያዊ እኩልነት ውጭ ማሰብ አይቻልም፡፡ ዘመኑ ተቀይሯል፡፡

ሁሌም ለለውጥ መዘጋጀት የግድ እየሆነ ነው፡፡ ርቀት እና ቆይታ በማንነታችን ላይ ተፅዕኖ እንዳይፈጥር ማሕበራዊ ካፒታል (ትስስር) አለኝታ ነው፡፡ ከአገር ቤት ጋር ያለንን ግንኙነትም በግልና በቡድን ማካሄድ ይቻላል፡፡ እነዚህን ለመጠበቅ የሚከተሉትን መርሆዎች መከተል ያስፈልጋል፡፡

ዲያስፖራው ከአገሩ ጋር ያለው ግንኙነት በፖለቲካዊ ፓርቲዎች አማካይነት መግለፅ አይገባውም፡፡ ዲያስፖራ ኢትዮጵያውያን የራሳቸው የፖለቲካ አመለካከት ያላቸው ቢሆንም ኑሯቸው በውጭ እስከቀጠለ ድረስ ንቁ የፖለቲካ ፓርቲ ተሳታፊ ሊሆኑ ስለማይችሉ የሚሰጡት ድጋፍ በአገራዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ በተለይ በልማት ዙሪያ ያነጣጠረ ቢሆን ይመረጣል፡፡

ማድረግ የሚቻለው የሚቻለውን ብቻ ነው፡፡ ዲያስፖራዎች በአገራዊ የጋራ ጉዳዮች ላይ ቢያተኩሩ እርስ በርስ መተማመን ይፈጠራል፡፡ በአገር ቤት ያሉት ተቋማትም ለዲያስፖራው የሚሰጡት አገልግሎት እየተጠናከረ ይሄዳል፡፡ የለም! በፖለቲካ ፓርቲዎች የግድ መሳተፍ አለብን የሚሉ ግለሰቦች ደግሞ ተሳትፏቸው ድጋፍ ከመስጠት ያለፈ መሆን የለበትም፡፡ በውጭ እየኖሩ ፖለቲካ ቡድን መስርቶ፣ መሪ ሆኖ በአገር ቤት ፖለቲካ ለመሳተፍ የሚደረግ ሙከራ አለመስራቱ ትናንት ታይቷል፡፡ ነገም የሚሰራ አይሆንም፡፡

በአገራችን ሕዝቦች መካከል ያለውን ግንኙነት በመቻቻልና በእኩልነት መርሆዎች ላይ እንዲሆን ብዙ ገድሎች ተካሂደዋል፡፡ በዲያስፖራው ውስጥ የሚገኙ ወገኖችም እነዚህ እሴቶች የአገራችን የፖለቲካ ባህል እንዲሆኑ ድጋፍ መስጠት አለባቸው፡፡ ከዴሞክራሲያዊ እኩልነትና ከመቻቻል ውጭ ኢትዮጵያን ማሰብ እንደማይቻል መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

አገራችን ላለፉት ጥቂት ዓመታት ፋታ በማግኘቷ የውጭ ሚዲያዎች ስለአገራችን አዎንታዊ ነገሮችን መዘገብ ጀምረዋል፡፡ በአገራችን የተጀመረው የዴሞክራሲ እና የሠላም መሠረት ሥር እየሰደደ ይሄድ ዘንድ የዲያስፖራ ድጋፍ ያስፈልገዋል፡፡ በዲያስፖራ አካባቢ የሚገኙ ፅንፈኞች በአገራችን የቀሰሩትን ጦረኛ ጣት ማጠፍ አለባቸው፡፡ የኢትዮጵያዊ ታሪካዊ ተቀናቃኞች መሣሪያ ሆነው በማገልገል ላይ የሚገኙ ወገኖችን በዲያሎግ መመለስ ካልተቻሉም መነጠል አለባቸው፡፡ ሠላም ሁሉም ዜጎች በጋራ የሚታገሉለት የጋራ አጀንዳ ነው፡፡

በዲያስፖራው አካባቢ የፅንፈኛው ሚዲያ የሚያሰራጨውን ነገር ለማወቅ በቅድሚያ መመርመር ያስፈልጋል፡፡ አንድን ነገር ተባለ ብለን ከመናገር በፊት ራስን መጠየቅ ተገቢ ነው፡፡ ይህ በአገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ሊሆን ይችላል ወይ? እንዴትስ ተናጋሪዎች መረጃውን ሊያገኙት ቻሉ? ይህን

ነገር የሚያስወሩ ሰዎች ዓላማቸው ምንድነው ? ብሎ መጠየቅ የግድ ይላል፡፡ ከአገራችን እና ከወገናችን ጋር ያለንን ሠላማዊ ግንኙነት ለመጠበቅ የሚቻለው ነገሮችን በመመርመር ስንረዳ ነው፡፡

የአገሬ ሰው ሌባው ሌባ! ሌባ! እያለ ይሮጣል የሚል አባባል አለው፡፡ የዛሬው ዘረኛም ቀድሞ ሌሎችን ዘረኛ! ዘረኛ! እያለ ከዲያሎግ መድረክ የሚሸሽ ነው፡፡ ዘረኛ ማለት በቀላሉ ሌላውን በእምነቱ፣ በቋንቋው፣ በቆዳው ቀለም የሚያገል ማለት ነው፡፡

በዲያስፖራው አካባቢ ያሉ ሚዲያዎች፣ የእምነት ተቋማት እና ስብስቦች ዘረኝነትን መወጋት ከቻሉ ዕድሜያቸውም ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በዘረኝነት የተሰነቁ አደረጃጀቶች ከጊዜያዊ እይታ ያለፈ ትርጉም የላቸውም፡፡ የዲያስፖራ ተቋማት ኢትዮጵያውያንን በሙሉ የሚያስተናግዱ ሆነው እንዲቀረፁ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ የመረባረብ ኃላፊነት ሊወስድ ይገባል፡፡

ቂምና ቁርሾ የአሁኑ ትውልድ አይገልፀውም፡፡ ቂምና ቁርሾ የአዛውንት ፅንፈኛ ፖለቲከኞች ባህርይ ነው፡፡ የዛሬው ትውልድ ከትናንቱ ዘመን ካለፈበት የፖለቲካ ሽኩቻ ራሱን መከላከል አለበት፡፡ አዛውንቶች ግን ሊተውት ይከብዳቸዋል፡፡ ሌላ ታሪክ የላቸውምና፡፡

አንዳንድ ወገኖች በምዕራቡ ዓለም የዴሞክራሲን ባህል በመርሳት ነፃ አስተሳሰብ ያላቸው ወገኖችን ለመነጠል ጥረት ያደርጋሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ መነጠል የነበራባቸው የግለሰብ ነፃነትን የሚጋፉ ወገኖች ነበሩ፡

እነዚህ ወገኖች ደርሰው ስለ ዴሞክራሲ የሚያወሩ ናቸው፡፡ ለእነዚህ ወገኖች "ጅብ በማያውቁት ሀገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ አለ" የሚለውን ተረት እስኪያጣጥሙት ድረስ ደጋግሞ በመንገር የግል ነፃነትን መጠበቅ ያስፈልጋል፡፡

በዲያስፖራው መካከል ቀጣይ ዲያሎግ ማካሄድ አስፈላጊ ነው፡፡ በኢትዮጵያውያን መካከል ያለው ማሕበራዊ ካፒታል ሊዳብር የሚችለው ዲያሎግ ማካሄድ ሲቻል ነው፡፡ የሚካሄደው ዲያሎግም በሰጥቶ መቀበል መርሕ ላይ የተመሰረተ መሆን ይገባዋል፡፡

አገራችን በፍጥነት እያደገች በመሆኗ የዚሁ የዕድገት ሂደት አካል መሆን ይገባናል፡፡ ባቡሩ ፈጣን በመሆኑ ትግሉ ከጊዜ ጋርም ጭምር ነው፡፡ ለአገራችን በምናደርገው ድጋፍ ላይ ብዙም መጨነቅ አያስፈልግም፡፡ በአሜሪካ አገር የሚኖር ኢትዮጵያዊ በቀን አንድ ዶላር ለአገሩ ቢያስብ ጉዳት ያለው አይመስለኝም፡፡

ከዚህ ባሻገር ለቤተሰብ የምንልከው ገንዘብ በሕጋዊ ባንክ ቢሆን ለአገርም ጭምር ይተርፋል፡፡ አቅም ያለው ወገን አገሩ ተመልሶ ኢንቨስት ቢያደርግ ይመከራል፡፡ ራሱ ተጠቅሞ አገርንም ይጠቅማልና፡፡

የዘመናችን ሰው የታደለ ትውልድ ነው፡፡ አባይን ለልማት ሲውል በማየቱ ብቻ ሳይሆን በግንባታው እንዲሳተፍ ዕድል በማግኘቱ ዕድለኛ ቢባል አይበዛም፡፡ ይህን ዕድል ቀደምቶች አላገኙትም፡፡ ተከታዩ ትውልድ ግን ቢያንስ በዚህ ትውልድ ይኮራል፡፡ ለታላቁ የህዳሴ ግድብ ያልሆነ ቀሚስ ይበጣጠስ!! እንዲሉ፡፡ የነገ ሰው ይበለን፡፡